በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የግብርና ሚኒስቴር

የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ

ኦዲት ሪፖርት

መጋቢት 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ

የግብርና ሚኒስቴር

የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

የግብርና ሚኒስቴር የተመደበለትን የመደበኛ እና የካፒታል በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የግብርና ሚኒስቴር ስራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው ::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣን ሲሆን ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶች ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣

- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል:: ከዚህም በተጨማሪ ኦዲቱ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑንና በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የግብርና ሚኒስቴር ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፤ መዛግብት፤ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በመ/ቤቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::
ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡
የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ማመዛዘኛ፣

ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፣

የግብርና ሚኒስቴር የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፤ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. በግብርና ሚኒስቴር በ2014 በጀት ዓመት በመ/ቤቱ ስር ላሉት መኪናዎች አመታዊ የተሽከርካሪ ቦሎ ምርመራ ለትራንስፖርት ባለስልጣን የቦሎ ምርመራ ክፍያዉን በወቅቱ ባለመፈጸሙ ምክንያት ተጨማሪ ክፍያ (ቅጣት) ብር 23,190.00 የተከፈለ መሆኑ፣
2. በሚዛን ኮሌጅ በገቢ ደረሰኝ ቁጥር 43030-43050 ከጨረታ ሽያጭ ገቢ ተጠቃሎ የተመዘገበው ብር 1,050.00 በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ ብር 4,050.00 ተመዝግቦ ሪፖርት በመደረጉ በልዩነት ብር 3,000.00 ያልተሰበሰበ ገቢ ተመዝግቦ ሪፖርት የተደረገ መሆኑ፣
3. በአርዳይታ ኮሌጅ የብር 37,397.17 ዋጋ ያለው 1,617 ሊትር ነዳጅ ገቢ ሳይደረግ አለአግባብ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣
4. የሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ በሚመለከተው አካል ሳይፈቀድ ለኮሌጁ መምህራን የቤት አበል በየወሩ ብር 600.00 በመክፈል በአጠቃላይ ብር 57,870.00 ከመመሪያ ውጭ የተከፈለ መሆኑ፣
5. በገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጁ በዋጋ ማወዳደሪያ የግዥ ዘዴ መሰረት የፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦ ለማጽዳት ከተወዳደሩት ሶስት ድርጅቶች መካከል ዝቅተኛ ዋጋ ያቀረበው የሱፍ ኡመር ብር 115,000.00 ሆኖ ሳለ በሁለተኛ ደረጃ ከፍተኛ ዋጋ ካቀረበው አብዱ ሳሊህ በብር 200,000.00 የአገልግሎት ግዥ በመፈጸሙ በልዩነቱ በብልጫ ብር 85,000.00 የተከፈለ መሆኑ፣

ተረጋግጧል፡፡

ከላይ በተራ ቁጥር 1 እና 5 ከተገለጸው በስተቀር የሚኒስቴሩ የሂሳብ ሪፖርቶች ሰኔ 30 ቀን 2014 ዓ.ም የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት ትክክለኛውን ገጽታ ያሳያሉ።

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡

I. <u>ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገባቸው ጉዳዮች (Emphasis of Matters)</u>

1.1 የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ዓ.ም. በክፍል ሁለት አንቀጽ 6 ተራ ቁጥር 4 ላይ የመንግስት መ/ቤቶች በበጀት አደረጃጀት ሥርዓት መሠረት የተፈቀደላቸው በጀትና የወጣው ወጪ በሚያሳይ መልኩ ተለይተው በተሰጡዋቸው የበጀት መለያ መደቦች ተጠቅመው የሂሳብ እንቅስቃሴያቸውን መመዝገብ እንዳለባቸው ይገልጻል ። ይሁን እንጂ ሚኒስቴሩ በዋናው መ/ቤት ብር 160,293.13 የሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ ብር 541,226.50 በድምሩ ብር **701,519.63** ወጪዎች በትክክለኛ የሂሳብ መደብ ያልተመዘገቡ መሆኑ፣

1.2 በየፕሮግራሞቹ ለየሂሳብ ኮዶቹ የተፈቀደው የመደበኛና የካፒታል በጀት ሥራ ላይ ከዋለው ጋር ሲነጻጸር ከ10% በላይ ከመደበኛ በጀት ብር 44,672,609.31 እንዲሁም ከካፒታል በጀት ብር 528,217,741.12 በድምሩ ብር 572,890,350.43 ሥራ ላይ ያልዋለ መሆኑ፣

1.3 በአርጻይታ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ ከግብርና ምርት፣ ከእንስሳት ተዋጽዖ፣ ከሲኦሲና ከተከታታይ ትምህርት የተሰበሰበውን ገቢ በዕለቱ ባንክ ገቢ ማድረግ ሲገባው በድምሩ ብር 186,134.30 (ከ5 — 17) ቀናት ዘግይቶ ገቢ የተደረገ መሆኑ፣

1.4 የግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማስተባበሪያ ዳይሬክቶሬት

- በቀን 24/02/14 በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 475255 ብር 12,765.00፣ በወጪ ማ.ቁ. 475257 ብር 29,555.00 እና በወጪ ማ.ቁ. 475256 ብር 24,150.00 በድምሩ ብር 66,470.00 ግዢ ሲፈጸም የዋጋ ማወዳደሪያ ሰንጠረዥ ቢቀርብም ተወዳዳሪዎች ያቀረቡት የእቃው አይነት እና የዋጋ ዝርዝር ማስረጃ ያልቀረበ ከመሆኑም በላይ የመኪና ታርጋ ቁጥር እና የመኪናውን ታሪክ የሚገልጽ ማስረጃ በሌለበት የመኪና እቃ ግዥ ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣
- ከፍተኛ ትምህርት ተቋሞቹ ይከፈለኝ ጥያቄ ለግብርና ሚኒስቴር ባቀረቡት መሰረት በተለያዩ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ የተፈቀደላቸው ሰራተኞች ስለመሆናቸው የተፈቀደበት ማስረጃ ፣ ሰራተኞቹ ትምህርታቸውን ለመከታተል የገቡት የውል ስምምነት ሳይቀርብ በድምር ብር 987,000.00 ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤

1.5 የሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ

- ለወጪ መሸፈኛ የሚውል የጥሬ ገንዘብ በካዝና መያዝ ከተፈቀደው የገንዘብ መጠን በላይ ብር 206,087.67 በየካቲት 30/2014 ሂሳብ ሪፖርት ላይ የተገኘ መሆኑ፣
- ከአምስት ሽህ ብር በላይ የቀን ውሎ አበል ክፍያ እና ለተማሪዎች ክሊኒክ ባለሙያዎች የዲውቲ ክፍያ በቼክ ወይም ወደ ባለመብቱ ሂሳብ ቁጥር (Account Transfer) መተላለፍ ሲገባው ከመመሪያ ውጭ ለእያንዳንዱ ሰራተኛ ከአምስት (5,000.00) ብር በላይ በድምሩ ብር 255,645.48 በጥሬ ገንዘብ (Cash) ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣

II. የህጋዊነት ጉዳዮች (Compliance Issues)

2.1 አጋርፋ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ የተለያዩ የዘርና ማዳበሪያ መዝሪያ ከጥላዬ ግዛዉ የእርሻ ሜካናይዜሽን የማሽነሪ ኪራይ የአገልግሎት ግዥ በማከናወን ክፍያ በሚፈፅምበት ጊዜ ብር 1,010,290.43 መከፈል ሲገባው የተጨማሪ እሴት ታክስ ተጨምሮ የተከፈለ መሆኑ፣

2.2 በሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ ብር 999,090.51 በአርዳይታ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ በድምሩ በብር 238,259.59 በጠቅላላው ድምር ብር 1,237,350.10 የተለያዩ የቋሚ እና አላቂ ዕቃዎችን በዋጋ ማቅረቢያ ግዥ ሲፈጸም በመመሪያው መሰረት በግዥ ስራ ክፍል የገበያ ጥናት በማድረግ ዝቅተኛ ተብሎ የሚመረጠው ዋጋ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ

2.5 መሆኑን አረጋግጦ ግዥ መፈጸም ሲገባው፤ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መሆኑን ሳይረጋግጥ ግዥ የተፈጸመ መሆኑ፣

2.6 ገዋኔ ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ በግልፅ ጨረታመፈጸም ሲገባው በመከፋፈል በዋጋ ማወዳደሪያ በድምር ብር 715,719.25 ከአንድ አቅራቢ ግዥ የፈጸመ መሆኑ፣

2.3 በዋናው መ/ቤት በድምሩ ብር 100,000.00 ከመመሪያው ውጪ ለድርጅቶች ድጋፍ የተደረገ መሆኑ፣

2.4 የሚዛን ግብርና ቴክኒክ ሙያ ትምህርት ስልጠና ኮሌጅ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ፈቃድ ሳያገኝ እና በቋሚ ሰራተኛ ማሰራት የሚገባውን መደቦች ማለትም የተማሪዎች ምግብ ቤት የግቢ ውበት ሰራተኛ እና አትክልተኛ ሰራተኛ ለረጅም ጊዜ በቀን ሰራተኛ የሚያሰራ ሲሆን፤ የቀን ሰራተኞቹ በትክክል ስለመስራታቸው ከሚመለከተው /ከአሰሪው የስራ ክፍል የፅሁፍ ማረጋገጫ ያልቀረበ መሆኑ ፣ የቀን ሰራተኛው ማንነቱን የሚገልጽ መታወቂያ ከወጪ ሰነዱ ጋር ሳይያያዝ በድምሩ ብር 680,924.50 ክፍያ የተፈጸም መሆኑ፣

2.7 ሰኔ 30/2014 በሚታየው ሂሳብ ሪፖርት በድምሩ ብር 86,013,456.16 ወቅቱን ጠብቆ ያልተሰበሰበ ሂሳብ መሆኑ፣ በተጨማሪ የተሰብሳቢ ሂሳቡ በእርጅና ዘመን እየተተነተነ ያልቀረበ መሆኑ፣

2.8 በድምሩ ብር 7,527,993.21 በወቅቱ ያልተከፈለ ውዝፍ ተከፋይ የተገኘ ከመሆኑ በተጨማሪ የተከፋይ ሂሳቡ በእርጅና ዘመን ተተንትኖ ያልቀረበ መሆኑ፣

III. <u>ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)</u>.

3.1 በግብርና ሚ/ር 11 ግዥ ሰራተኛ፣ 44 ሹፌሮች፣ 17 የንብረት ሠራተኞች እና 62 የጥበቃ ሰራተኞች በመመሪያው መሰረት በቂ ዋስትና ማቅረብ ሲገባቸው ያላቀረቡ መሆኑ፣

3.2 ለግብርና ሚ/ር ሰራተኞች ለሚጠቀሙባቸው መደበኛ ስልኮች በሥራ አመራሩ የተወሰነ ወርሃዊ የስልክ ጣሪያ አለመኖሩ ታውቋል፡፡

<u>የቋሚ ንብረቶች በተመለከተ፤</u>

- ✓ በቃሊቲ ግቢ ውስጥ ሜዳ ላይ 9 የቦቆሎ መፈልፈያ ንብረትነቱ የፕሮጀክት የሆነ ከ2 ዓመት በላይ ያለስራ ቆመው የሚገኑ መሆኑ፤ 5 ምን እንደሆነ የማይታወቅ በእንጨት የተሰራ ሳጥን ንብረት የያዙ ሳጥኖች፤ 4 ጥቅል የውሀ መሳቢያ ቱቦ (ፓይፕ) ሜዳ ላይ ያለአግባብ የተቀመጠ መሆኑ፤ እንዲሁም ቁጥሩ በዉል የማይታወቅ ከብረት የተሰራ የጨፍ በመስመር መዝሪያ ማሽን ለረጅም ጊዜ እልባት ሳያገኝ ባልተገባ ሁኔታ ሜዳ ላይ የሚገኝ መሆኑ፤ የንብረት መጋዘኖች ቬንትሌተር እና የእሳት ማጥፊያ የሌላቸዉ እና ያሉትም የማይሰሩ መሆኑ፤
- ✓ በቃሊቲ የተመላሽ ስቶር ውስጥ ብዛት ያላቸው የተለያዩ መጽሃፎች፤ የሂሳብ ሰነዶች እና የሰው ሃብት ማስረጃዎች በማዳበሪያ ተደርጎ ባልተገባ መንገድ የተቀመጠ መሆኑ፤ ብዛት ያላቸው ቶነሮች፤ ላፕቶፕ፤ በካርቶን የተቀመጡ አዲስ ከለር ወረቀቶች፤ ለመለየትና ለማየት ያልተቻሉ የተለያዩ ንብረቶችና ሰነዶች በስቶር ውስጥ ተደበላልቀው የሚገኝ መሆኑ፤ እንዲሁም ለሌላ ተቋም የተላለፉ ንብረቶች ወጪ ሳይደረጉ በስቶር ውስጥ ለተመልካች በማይሰብ መልኩ የተቀመጠ መሆኑ፤
- ✓ በዚሁ የተመላሽ ስቶር ውስጥ ሦስት(3) የቅኝት/ሰርቬ ድሮን የሚገኝ መሆኑ እንዲሁም ወደ ተመላሽ ስቶር ገቢ የተደረገበት መንገድ ግልጽ ያለመሆኑ፤ አንድ ስሙ የማይተወቅ ማሽን ያለ ርክክብ ሰነድ ስቶር ውስጥ የሚገኝ መሆኑ፤ ብዛት

- ✓ ያላቸዉ የኤሌክትሮኒክ ዕቃዎች፣ ቶነሮች፣ ላፕቶፕና ፎቶኮፒን ጨምሮ ብዛት ያላቸዉ የኤሌክትሮኒክ ዕቃዎች መሬት ላይ ያላግባብ ተበትነዉ የሚገኙ መሆኑ፣
- ✓ በሌላ አንድ የተመላሽ ስቶር ውስጥ (ቃሊቲ) በርካታ ኮምፒውተሮች ከዋናው መ/ቤቱ የመጡ ናቸው በሚል ያለ ርክክብ የሚገኙ መሆኑ፣ የኮምፒውተሮችም አቀማመጥ ለብልሽት በሚዳርግ ሁኔታ የተቀመጡ መሆኑ፣ በዚሁ ስቶር ውስጥ ያሉ ተመላሽ ንብረቶች በተለይ ኮምፖዊተሮችና ፕሪንተሮች ስለ መስራታቸውና አለመስራታቸው በባለሙያ በጹሁፍ የማይረጋገጥ መሆኑ፣ ስቶር ውስጥ አመታትን ያስቆጠሩ የተለያዩ ንብረቶች ለመለየት በሚያስቸግር ሁኔታ የሚገኙ መሆኑ፣
- ✓ በቃሊቲ የእንስሳት መድሃኒት እና መገልገያ ስቶር ውስጥ በ2007 ዓ.ም ገቢ የተደረገ የእንስሳ የጆሮ ታግ ብዛቱ 206,700 ፣ የበግና የፍይል የጆሮ ታግ ብዛቱ 19,200.00 ፣ የጆሮ መብሻ ብዛቱ 671 ፣ የእንስሳስ መርፌ መውጊያ ብዛቱ 5,184.00 ፣ ከመሬት አስተዳደር የተገኘ ሁለት አዲስ ኤች ፒ ኤም 426 ዲ ዳብሊው ፕሪንተር፣ 2 ኤች ፒ ኮራይ 5 ላፕቶፕ ፣ ሁለት የፊልድ ቦርሳና ሦስት ማይክራፎን በስቶር ውስጥ የሚገኝ መሆኑ፣ በዚሁ ስቶር ውስጥ ብዛቱ 11 የሆነ ማረሻና መኮትኮቻ ከጂአይዚድ የመጣ፣ በ2013 ገቢ እንደተደረገ የተነገረን የአነስተኛ መስኖ ውሃ ማውጫ ድሪል/ማሽን/፣ እንዲሁም ብዛቱ 5 የሆነ 1,000 ሊትር ውሃ የሚይዝ ታንከር ከውጪ ያለምንም ከለላ የተቀመጠ መሆኑ በኦዲት ምልከታ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

<u>ኬሚካልን በተመለከተ፣</u>

- ✓ በቃሊቲ ግቢ ውስጥ ከሚገኘው የኬሚካል ስቶር ውስጥ 42,000 ሊትር 45 ፐርሰንት ክሎሮፋይረስ የአንበጣ መከላከያ ኬሚካል የአገልግሎት ዘመኑ የማይታወቅ የሚገኝ መሆኑ፣
- ✓ 48,000 ሊትር 92.5 ፐርሰንት ማላታይን የአንበጣ መከላከያ ኬሚካል ከፋኦ የመጣ እንዲሁም 181 በርሚል 95 በመቶ ማላታይን የሆነ የአንበጣ መከላከያ ኬሚካል የአገልግሎት ዘመኑ ያለፈበት በስቶር ዉስጥ የሚገኝ መሆኑ፣
- ✓ 30 በርሚል ማላቲያን ከአዳሚ ቶሉ የተገዛ ነገር ግን ለንብ ጠንቅ በመሆኑ በሚል ያለአገልግሎት ተቀምጦ የሚገኝ መሆኑ፣

- ✓ ጥቅም የማይሰጡ የአገልግሎት ዘመናቸው ያለፈባቸው ከ4 በርሚል በላይ እንዲሁም በተላያዩ ጀሪካኖች የተቀመጡ ኬሚካሎች ሜዳ ላይ የሚገኙ መሆኑ፤ እንዲሁም ለስራ ወጪ ተደርገው ወደ ተለያዩ ክልሎች ተወሰደው የነበሩ የተለያዩ ኬሚካሎች ተመላሽ ሲደረጉ ያለምንም ተመላሽ ሰነድ ሜዳ ላይ ለአግባብ ተቀምጠው የሚገኝ መሆኑ፣
- ✓ ብዛቱ 45 የሚሆን ተገጣጣሚ የጢንዚዛ ወጥመድ ከ15 አመት በላይ ስራ ላይ ሳይውል አዲስ እንደሆነ የሚገኝ መሆኑ፤ ብዛቱ ከ15 በላይ የሚሆን የመስክ ስራ ላይ የሚውል አዳዲስ ድንኳን ያለ አገለግሎት ከ20 አመት በላይ የተቀመጠ መሆኑ፤ በደርግ ዘመነ መንግስት የመጣ በባይሎጂካል መንገድ አይጦችን የሚያጠፋ ማሽን ያለ አገልግሎት በስቶር የሚገኝ መሆኑ፣
- ✓ 2 የእጽዋት ላብራቶሪ ማሽን ከነመለዋወጫው 2013 ጀምሮ እንደገባ የተገለጸልን ሜዳ ላይ የሚገኝ መሆኑ፣
- ✓ አንድ የኬሚካል ስቶር በመሆን የሚያገለግለው ስቶር ቆርቆሮ በቆርቆረ መሆኑ ለኬሚካሉና ለስራው አስቸጋሪ መሆኑ፣
- ✓ ቃሊቲ የሚገኘው የሰነድ ክፍል ውስጥ በርካታ ሰነዶች የሚገኙ ሲሆን ስቶሩ ቆርቆሮ በቆርቆሮ ከመሆኑ በተጨማሪ ከላይ ቆርቆሮው የሚያፈስ በመሆኑ ሰነዶቹ ለብልሽት እየተዳረጉ መሆኑ

በኦዲቱ ታውቋል፡፡

<u>ሳሪስ ግቢ፤</u>

- ✓ በሳሪስ ግቢ ሜዳ ላይ አንድ/1/ የዘር መዝሪያ የተበላሸ፤ አዲስ የበቆሎ መፈልፈያ ብዛት 9 ከ3 አመት በላይ ሜዳ ላይ የተቀመጠ፤ አንድ የጤፍ መውቂያ እንዲሁም አንድ እያጨደ የሚፈጭ ሜዳ ላይ የሚገኙ መሆኑ፤ የግብርና መካናይዜሽን ወሰዶት የነበረ ትልቁ ኮምባይነር ያለ ርክክብ ሜዳ ላይ መሆኑ፤ ከጀርመን የመጣ አንድ አዲስ የውሃ ቦይ የሚያወጣ ማሽን ገቢ ሳይደረግ ሜዳ ላይ የሚገኝ መሆኑ፤ 8 አዲስ ማረሻ ትራክተር ከ3 አመት በላይ ሜዳ ላይ የተቀመጠ መሆኑ፤ ከሞኢንኮ

- ✓ የተገዛ 5 አዲስ ማረሻ በሜዳ ላይ የሚገኝ መሆኑ፤ 8 አዳዲስ ማረሻ በትራክተር የሚጎተት ከ3 አመት በላይ ሜዳ ላይ የሚገኝ መሆኑ፣
- ✓ በሳሪስ ቋሚ ስቶር ውስጥ 6 የአሳ መረብ፣ 13 የወረቀት መብሻ፣ ብዛቱ የማይታወቅ hp ቶነሮች፣ ብዛቱ የማይታወቅ hp ሊዘር ጀት ፕሪንተሮች፣ ከ351 ሳምሰንግ ጋላክሲ Tab s6 lite ከ2 ዓመት በላይ ያለስራ የተቀመጡ መሆኑ፣
- ✓ በዚሁ ስቶር ውስጥ 11 አዲስ ኤር ኮንዴሽነር፤ አዲስ 1 ፎቶ ኮፒ እስከ እስካነሩ፤ 4 አዲስ የእሳት ማጥፊያ /መቆጣጠሪያ/፤ 320 ፕሮጀክተር፤ 4 አዳዲስ የተለያዩ የሰርቨር እቃዎች፤ 1,227 ኮምፓስ፤ ዲስክ 320 hp ሌዘር ጀት ፕሪንተር፤ 320 smart UPS C፤ 3 ባለእንጨት የሰርበር ማስቀመጫ ንብረቶች ወደ ስቶር በንብረት ገቢ ደረሰኝ ገቢ ሳይደረጉ በስቶር የተገኙ መሆኑ በኦዲት ወቅት ታውቋል፡፡
- ✓ በሳሪስ በሌላ አንድ የአላቂ እቃ ስቶር ውስጥ ብዛቱ 656 የሆነ የመስታውት ማጠቢያ የአገልግሎት ጊዜዉ እንደ እ.ኤ.አ በ2019 ያለፈበት በስቶር ዉስጥ በካርቶን ተቀምጦ የሚገኝ መሆኑ፤ ብዛት ያላቸው የተለያዩ የፕሮጀክት መጽሐፍቶች፤ ብዛት ያላቸው የሂሳብ እና የንብረት ደረሰኞች ማለትም የቫት፤ የወጪ፤የገቢ ደረሰኞች፤ የተለያዩ መሂዎች እና ሞዴሎች በስቶር ዉስጥ የሚገኙ መሆኑ፤ ብዛት ያለው የወረቀት/የማስታወሻ ማስቀመጫ፤ ቁጥሩ የማይታወቅ የብሮጀክት የከለር ቶነር ከ4 አመት በላይ ያለ አገልግሎት የሚገኝ መሆኑ፤ የእንሰሳትና ዓሳ ሀብት ሚኒስቴር ንብረት የነበረ 127 ማስታዎሻ ደብተር፤ 2 UPS፤ 16 ትልቁ ፓንቸር፤ 18 ፍላሽ ዲስክ 1 እና 2 ጂቢ፤ 36 ማርከር ቀጭን፤ 2,403 ትልቁ ካኪ ፖስታ፤ 4,600 መካከለኛ ካኪ ፖስታ፤ እና ሌሎች እቃዎች መቼ እንደገቡ በውል የማይታወቁ ንብረቶች በስቶር የሚገኙ መሆኑ፤ በተጠቀሰው ስቶር ውስጥ 81 የዕቃ ወጪ ማድረጊያ ጥራዝ፤ 4,492 ቀይ እስክርቢቶ፤ 12 የፕሪንተር ቀለም Hp 711፤ 3278 network cable የመሬት ፕሮጀክት የሆነ፤ 4738 ኢንተርኔት cable የመሬት ፕሮጀክት እና ሌሎች እቃዎች የሚገኙ መሆኑን በቢን ካርድና በስቶር ለማየት ተችሏል፡፡

ተሽከርካሪን በተመለከተ፤

- ✓ በቃሊቲ ግቢ ውስጥ 76 የተለያየ አይነት ተሽከርካሪዎች የሚወገዱ በሚል ሜዳ ላይ ያለ መጠለያ የሚገኙ መሆኑ፣
- ✓ 1 አዳኖ /ADANO/ ክሬን 230 ቶን የሚያነሳ ከ4ዓመት በላይ ዝናብና ጸሀይ እየተፈራረቀበት የሚገኝ መሆኑ፤ 2 የሚወገዱ /አገልግሎት የማይሰጡ/ ሞተር ሳይክሎች ኮድ 0904 እና ዕድ 39-002 ከስቶር ዉጪ ለረጅም ዓመታት በቃሊቲ እጥር ግቢ ዉስጥ የቆሙ መሆኑ፣
- ✓ በሳሪስ ግቢ ውስጥ ብዛታቸው 45 የሆነ አዳዲስ ሞተር ሳይክሎች ሜዳ ላይ ያለ ሼድ የሚገኙ መሆኑ፣
- ✓ በሁሉም ምልከታ በተደረገባቸው ስቶሮች ውስጥ የእሳት ማጥፊያ የሌለ መሆኑ፤
- ✓ እንደ መ/ቤቱ አመታዊ የንብረት ቆጠራ በ2012፤ በ2013 እና በ2014 ዓ/ም ቆጠራ ያልተደረገ መሆኑ፣
- ✓ ግዢ ከመከናወኑ በፊት የሚገዛው ንብረት ስቶር ውስጥ ስለመኖሩ ከስቶር ክፍል ሰራተኛው በጹሁፍ መረጃ የማይጠየቅ መሆኑ፣
- ✓ ከአንድ ስቶር ውጪ በአብዛኛው ስቶር ውስጥ ቢን ካርድ የሌለ መሆኑ፤ያሉትም ቢን ካርዶች ትክክለኛ የንብቱን መረጃና ባላንስ የሚያሳይ መሆኑ፤ በኦዲቱ ተረጋግጧል፡፡

1. የመ/ቤቱን የተሽከርካሪ ሥምሪት፤ አያያዝና አጠቃቀም በፌደራል መንግሥት የተሽከርካሪዎች ስምሪትና አጠቃቀም መመሪያ ቁጥር 32/2004 መሰረት መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- በመ/ቤቱ 20 ተሽከርካሪዎች በመ/ቤቱ ስም የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር የሌላቸው መሆኑ በኦዲቱ ታወቅቋል፡፡
2. የፌዴራል ዋና ኦዲተር ከ2009 እስከ 2014 በጀት ዓመት ሂሳብ መግለጫዎችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርጎ ሙያዊ አስተያየትና የማሻሻያ ሃሳቦች ያቀረበ ሲሆን፣ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ የተወሰደባቸውና ያልተወሰደባቸው ግኝቶች ሁኔታ ሲጣራ፡-

I. የ2013 በጀት አመት የሂሳብና የንብረት ኦዲት ግኝቶች፤

1. በተለያዩ የተከፋይ ሂሳብ ኮዶች ክሬዲት ሚዛን መታየት ያለበት ቢሆንም በጠቅላላው ብር 2,064,307.67 ዴቢት ሚዛን የሚታይ መሆኑ የታወቀ ሲሆን በ2009, በ2010, በ2011 እና በ2012 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ወቅት ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ አስተያየት የተሰጠበት ቢሆንም ሁኔታው ተጣርቶ ተገቢው ማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ፤ (ዝርዝሩ በአባሪ 9 ተመላክቷል፡፡)

II. የ2012 በጀት ዓመት የሂሳብና የንብረት ኦዲት ግኝቶች፤

1. በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ይሰሩ የነበሩ ሶስት ሠራተኞች ከሥራ በለቀቁበት ወቅት ለሥራ የተረከቧቸውን ቋሚ ዕቃዎች ወደ ሌላ ሰራተኛ ወይም የሥራ ክፍል በርክክብ ሳያስተላልፉ ወይም ለንብረት ክፍል ተመላሽ ሳያደረጉ ንብረቶቹ በሰራተኞቹ ሥም ብር 737,850.85 የሚያወጡ ንብረቶች የሚገኙ መሆኑ፤ ዝርዝራቸውም፡-
   - 1.1. አቶ ንጉሴ ገረሱ በስማቸው በቋሚና በአላቂ ንብረቶች መቆጣጠሪያ ካርድ (User Card) ላይ ተመዝግቦ ከተረከቡት ንብረት ውስጥ ተመላሽ ሳይደረግ ከቀረው ብር 17,435.17 ውስጥ በ2014 በጀት አመት ኦዲት ብር 16,120.94 ማስረጃ የቀረበለት ሲሆን ቀሪው ብር 1,314.23 ማሰረጃ ያልቀረበ መሆኑ፤
   - 1.2. አቶ ሆነልኝ እንዳለው በስማቸው በቋሚና በአላቂ ንብረቶች መቆጣጠሪያ ካርድ (User Card) ላይ ተመዝግቦ ከተረከቡትን ንብረት ውስጥ ተመላሽ ሳይደረግ ከቀረው የብር 3,576,610.00 ንብረት ውስጥ በ2014 በጀት አመት የብር 3,424,610.00 ዋጋ ያለው ንብረቶች ተመላሽ ያደረጉበት ማስረጃ ያቀረቡና ያረጋገጥ ሲሆን ቀሪው የብር 152,000.00 ዋጋ ያለው ንብረት ተመላሽ ያልተደረገ መሆኑ፤

1.3. አቶ ደረጀ ዋቅጅራ በስማቸው በቋሚና በአላቂ ንብረቶች መቆጣጠሪያ ካርድ (User Card) ላይ ተመዝግቦ የሚገኘውንና የተረከቡትን የብር 574,536.62 ቋሚ እቃዎች ተመላሽ ለማድረጋቸው ማስረጃ ያልቀረበለት መሆኑ፣

III. <u>የ2009 በጀት ዓመት የሂሳብና የንብረት ኦዲት ግኝቶች</u>፤

1. የቀድሞው የእርሻና ተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር ዴኤታ የነበሩት የአቶ ወንድራድ ማንደፍሮ ጥቅማ ጥቅሞች በበጀት ዓመቱ በተሰላው መሰረት፡-

   - ✓ የመቋቋሚያ አበል ብር 128,601.00፣
   - ✓ የመኖሪያ ቤት አበል ብር 120,000.00፣
   - ✓ የተሽከርካሪ አበል ብር 22,572.00፣

   በጠቅላላ ከተፈጸመው ብር 271,173.00 ክፍያ ላይ ብር 93,410.55 የሥራ ግብር መቀነስ ሲገባው ብር 49,910.55 ብቻ በመቀነሱ ብር 43,500.00 የሥራ ግብር ያልተቀነሰ መሆኑ፤

የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት

መጋቢት 2015 ዓ.ም